## ትግሉንና ድሉን የጋራ በማድረግ መርህ ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ለሃገራችን የወደፊት እጣ ፋንታ ወሳኝ ነው!

### የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ ለህዝብ ክፍት የሆነ አለም አቀፍ ጋዜጣዊ መግለጫ

ቀን፥ 9/5/2015 እ.አ.አ.

የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ በኢትዮጵያ የስደት መንግስት የምስረታ ሂደትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ማብራሪያ ለመስጠት፤ **ቅዳሜ፣ ሴፕቴምበር 12፣ 2015 ከቀኑ 3pm** ጀምሮ (በዋሽንግተን ዲሲ ሰአት አቆጣጠር) ለህዝብ ክፍት የሆነ አለም አቀፍ ጋዜጣዊ መግለጫ አዘጋጅቷል። በእለቱ የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ ተወካዮች፤ የስደት መንግስት ምስረታው ሂደቶችንና የተከናወኑ ተግባራትን በዝርዝርና በጥልቀት ከማቅረባቸውም ባሻገር፤ በሚዲያ ተወካዮችና የተለያዩ በርካታ ተካፋይ ጋዜጠኞች ለሚነሱ ማንኛውም ጥያቄዎች ግልፅ በሆነ መንገድ ማብራሪያዎችን ይሰጣሉ።

ሁሉም ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቀው፤ የኢትዮጵያ የስደት መንግስት ምስረታ አስተባባሪ አባል ተቋማትና ድርጅቶች መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት ድርጅቶች፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክርቤትና የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ ነሃሴ 21፣ 2015 ቀን የስደት መንግስት የመመስረቱ ሂደትን መጀመር ለህዝብ ይፋ ለማድረግ፤ በጋራ ባወጡት የአቋም መግለጫ ላይ የስደት መንግስቱን አስፈላጊነት ለማስገንዘብ፥ "የኢትዮጵያ የስደት መንግስት የመጨረሻ ግብ የሚሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ የተረጋጋና ወደዘለቄታዊ ሰላም የሚያመራ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር መኖሩን ማረጋገጥ ነው። ያልታቀደ የስርዓት ለውጥ የሚያስከትለውን ቀውስ ለመገንዘብ በሃገራችን ታሪክ ያለፍናቸው የለውጥ ሂደቶችን መመልከት በቂ ነው። በተጨማሪም በየመን፣ በግብጽ፣ በሊቢያና፣ በሶሪያ እየሆነ ያለውን መመልከትም እንችላለን። ይሁንና ህዝባችን የተማከለ አመራር የሚሰጥና የሚመካበት አማራጭ ኃይል እውን ሆኖ ማየት ካልቻለ፤ ፈጠነም ዘገየም አምባገነኑ የህወሓት/ኢህዴግ ቡድን መገርሰሱ፤ ለውጥም መምጣቱ የማይቀር ሃቅ ነው። በየትኛውም ሀገር አምባገነን ስርዓት እስካለ ድረስ ህዝብ ማመጹ፥ ለውጥም መምጣቱ አይቀሬ ነው። ሃገራችን ኢትዮጵያም ከዚህ ሃቅ የተለየ ሊገጥማት ስለማይችል፤ ሌላ ቀይ ሽብር፣ ሌላ አፓርታይድ ስርዓት፣ ሌላ የህዝብ እልቂት በሀገራችን ዳግም እንዳይከሰት፤ የሚመጣው የለውጥ ሂደት በተረጋጋና በተቀናጀ መልኩ እንዲያልቅ እንፈልጋለን፤ እንታገላለን።" ብለዋል።

ይህ ጋዜጣዊ መግለጫም ይህንኑ ታሳቢ ያደረገና በቀጥታ የስልክ መስመር የሚተላለፍ ለህዝብ ክፍት የሆነ ወሳኝ ታሪካዊ መድረክ ነው። በመሆኑም ለመላው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን፣ ለሚዲያ ተቋማት፣ ለጋዜጠኞች፣ ለፓልቶክ ክፍሎች፣ ለድህረ ገጾችና፣ ሌሎች ማንኛውም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ለሚሉ ተቋማትና ግለሰቦች፤ ይህ መድረክ በሃገራችን ታሪክ ልዩና ወሳኝ መሆኑን ተረድታችሁ፤ በተለይ በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ኢትዬጵያ የህዝብ ውክልና ያለው መንግሥት እንደሌለ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ መሆኑን በማስመር፤ ይህንን አምባገነን ሥርዓት ሁሉን አቀፍ በሆነ የተቀናጀ ትግል የሚያስወግድ የእዝ ማዕከል ሊሆን የሚችል የስደት መንግሥት መመሥረት ለሃገራችንና ለህዝቧ የወደፊት እጣ ፈንታ መሰረት የምንጥልበት ወሳኝ እድል መሆኑን ተገንዝባችሁ፤ የዚህ ታላቅ ታሪካዊ መድረክ ተካፋይ እንድትሆኑ ሲል የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ ሃገራዊ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል።

ቀን፥ **ቅዳሜ፣ ሴፕቴምበር 12፣ 2015**
ሰአት፥ **3PM (በዋሽንግተን ዲሲ ሰአት አቆጣጠር)**

የዝግጅቱ ተካፋይ ለመሆን ከታች ከተዘረዘሩት የስልክ ቁጥሮች አንዱን መርጠው በመደወል፤ ይህን የመግቢያ ቁልፉ (code): **468969#** ይምቱ።

International access phone numbers:
Australia +61 (0) 3 8672 0105
Belgium +32 (0) 4 244 10 83
Canada (641) 715-3803
Denmark +45 78 77 21 83
France +33 (0) 1 80 14 00 06
Germany +49 (0) 69 1200650760
Israel +972 (0) 76-599-0022
Italy +39 011 092 0917
Kenya +254 (0) 20 5231048
Netherlands +31 (0) 6 35205032
Norway +47 21 93 06 45
South Africa +27 (0) 87 825 0106
Sweden +46 (0) 8 124 107 12
Switzerland +41 (0) 44 513 30 30
United Kingdom +44 (0) 330 606 0515
United States +1 605 562-3140

ለበለጠ መረጃ: geeocpr@gmail.com

**ኑ የሃገራችንን የወደፊት እጣ ፋንታ በጋራ እንወስን!**

**የኢትዮጵያ የስደት መንግስት አደራጅ ኮሚቴ**